የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፱ኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ–ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 17
ADDIS ABABA–10th December, 2002

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፭/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
ላልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፩ሺ፱፻፸፭

CONTENTS

Proclamation No. 305/2002
International Development Association Credit Agreement for Financing Capacity Building for Decentralized Service Delivery Project Ratification Proclamation ........................................ Page 1975

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፭/፲፱፻፺፭
## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ላልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር· ፳ ሚሊዮን ፯፻ሺ ህ (ሃያ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ኤስ·ዲ·አር·) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፲፪ ቀን ፪ሺ፪ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ላልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር የተገኘው ብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፭/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION No. 305/2002
## *A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION*

WHEREAS, a Credit Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that International Development Association provide to the Federal Demcoratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR. 20,700,000 (twenty million seven hundred thousand Special Drawing Rights) for financing Capacity Building for Decentralized Service Delivery Project, was signed in Washington D.C on the 12th day of September, 2002;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its Session held on the 10th day of December, 2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for Financing Capacity Building for Decentralized Service Delivery Project Ratification Proclamation No. 305/2002."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፲፪ ቀን ፪ሺ፪ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመው ቁጥር ፫ሺ፮፻፺፰–ኢት· የብድር ስምምነት ነው።

፫· <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ·ዲ·አር· ፳ ሚሊዮን ፯ መቶ ሺ (ሃያ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር·) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Credit Agreement" means the Credit Agrrement Number 3698-ET signed in Washington D.C. on the 12th day of September, 2002, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR. 20,700,000 (twenty million seven hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 10th day of December, 2002.

Done at Addis Ababa, this 10th day of December, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE